# ከተራራው ጫፍ የወረዱት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ
# ያልታሰበ የተቃውሞ ማዕበል በቶሮንቶ ገጠማቸው

የአፈንጋጩ ቡድን አባል፣ ከማንኛውም የቅንጅት እንቅስቃሴ የታገዱትና "ተራራ ጫፍ ላይ ቁጭ ብዬ አስባለሁ" ሲሉ የነበሩት ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የቅንጅትን ፓርቲ እገዳ በመጣስ በቶሮንቶ የተለጣፊው ቡድን በቅንጅት ስም በጠራቸው ስብሰባ ላይ ለመገኘት ቅዳሜ ኤፕሪል 19 ቀን 2008 ዓ.ም **40 Donlands Avenue** በሚገኘው የግሪክ ቤተክርስቲያን ምድር ቤት ወደ ስብሰባ ለመግባት ከቦታው ሲደርሱ የገጠማቸው ከፍተኛ የተቃውሞ ድምጽ ቀዝቃዛ ላብ በጀርባቸው እንዲወርድ ያደረገና ድንጋጤ እንደፈጠረባቸው ከቶሮንቶ የተገኘው ዜና ያመለክታል።




አሜሪካ አገር የለመዱት ጉሮ ወሸባዬ ዘፈንና አቀባባል ቶሮንቶ አልተደረገላቸውም፤ በተቃራኒው ከፍተኛ የተቃውሞ ድምጽ ገጥሟቸዋል። ያልተጠበቁት ሁኔታ በመሆኑ ምነው እዛው ከተራራው ጫፍ በቆየሁ እንዳሰኛቸውና ወደ ቶሮንቶ ለመምጣት የወሰኑበትን ቀን ሳያስረግማቸው እንዳልቀረ ተገምቷል።



## DR. BERHANU NEGA BETRAYED THE ETHIOPIAN PEOPLE

## ቅንጅት አንድ ነው

እና ሌሎችም የተለያዩ መፈክሮች የተያዙ ሲሆኑ ሰልፈኞቹ ዶክተር ብርሃኑ ሲገቡ መፈክሮችን በማሰማትና የተቃውሞ ድምጽ በማሰማት ውር ውር ሲሉ የነበሩ ደጋፊዎቻቸው ከፍተኛ መደናገጥ ይታይባቸው እንደነበር ተስተውሏል። አንዳንዱም ፊቱ እያዞረ ሲመለስ ሌላውም መኪናውን እያዞረ ወደ መጣበት ተመልሷል።

ሌላው በሰልፉ ላይ የተከናወነው ድርጊት፣ የዶክተር ብርሃኑ ነጋ "የነጻነት ጎኅ ሲቀድ " በሚል ከቃሊቲ ተጻፈ የሚለው መጽሐፍ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በመጽሐፉ ይዘትም ሆነ መጽሐፉ ተሸጦ ለትግሉ ይውላል የተባለው ገንዘብ ባለመዋሉ የመጽሐፉን ዋጋ ቢስነትና የኪስ ማደለቢያ መሆኑን በማሳወቅ መጽሐፉ ተቀዳዶ በተገቢው ቦታ ማለትም ወደ ቁሻሻ መጣያ እንዲጣል ተደርጓል።




ቶሮንቶ የአንድነት ኃይሉ ክፍል ጠንካራና የማይበገር መሆኑን ከማስመስከሩም በላይ፣ የቅንጅት አመራር ወደ ካናዳ እንዳይገቡና ከኢትዮጵያውያን ጋር እንዳይገናኙ ቪዛ መከልከላቸው ለምን እንደሆነ ግልጽ ብሎ የታዬ ሲሆን በአንጻሩ ካለው መንግሥት ጋር የሚሞዳሞዱት እንደልባቸው ሲገቡና ሲወጡ መታየቱ አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ የሚያንገበግበው ጉዳይ በመሆኑ ላለው መንግሥት የሚያጎበድዱ እና የውጭ ኃይል መሳሪያ የሆኑትን በማጋለጥና በማውገዝ አይበገሬነቱን ዛሬም አስመስክሯል።



የቶሮንቶው ተለጣፊ ቡድን በጠራውና ዶክተር ብርሃኑ ነጋ የተገኙበት አዳራሽ በዚህ ምድር ቤት ውስጥ ነበር። በስብሰባው ላይ የተገኘው የሰው ቁጥር ከአርባና ሃምሳ የማይበልጥ ሲሆን ጥያቄ ለመጠየቅና ምን እንደሚል ለመስማት በእራት ዝግጅቱ ላይ ሃያ ሰው ብቻ እንደተገኘ ታውቋል። በገዛ እጁ ቶሮንቶ መጥቶ ተዋረደ ብለው አንድ ተሳታፊ ሲናገሩም ተደምጧል።

በስፍራው ሲደርሱ "ባንዳ ባንዳ ባንዳ " የሚል ያልተቊረጠ ድምጽ በመስማታቸው ተደናግጠው እጃቸውን በድንጋጤ አውለውልበው ወደ ቤዝመንቱ ወርደዋል፡፡ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥም ጆሯቸው ውጭ ስለነበር " እ ምን አሉ? ባንዳ ነው የሚሉት" ሲሉም ተሰምተዋል፡፡ ስብሰባውን አቊርጠውም ወደ ሽንት ቤት ጎራ ማለታቸው ድንጋጤው የሆድ ሕመም ችግር ሳይፈጥርባቸው እንዳልቀረ በስፍራው ከነበሩ ሰዎች ተደምጧል፡፡

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከህሊናቸው ዘወትር የማይጠፋውን ትምህርት ከሰጠና የሕዝብን ትግል የከዳ በሄደበት የሚዋረድና የሚጋለጥ መሆኑን የቶሮንቶ ተቃዋሚ ካስመዘገበ በኋላ ከቀኑ አስር ሰዓት ላይ በሰላም ተበትኗል፡፡

እየተወናበዱ ግራ የመጋባት ዘመን አልፏል፡፡ ማን ሀቀኛ፡ ማን ከፋፋይና ትግሉን የሚያዳክም፣ ማን ደግሞ ከጠላት እንደወገነ ከታወቀ ተቃዋሚው ደግሞ ተገቢውንና ትክክለኛ አቋሙን ማንጸባረቅ አለበት፡፡ የታጋዮች ሡፈር በባንዳ አይወረርም የሚል ጽሑፍ በቅርቡ ወጥቶ ነበር አዎን የታጋዮች ሡፈር በባንዳ አይወረረም፡፡ ቶሮንቶ የባንዳዎች መጨፈሪያ አይሆንም፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !
ቅንጅት አንድ ነው!
የአንድነት ኃይሉ ይጠናከራል!